# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 131 ህዳር 9 ቀን 2003 ገጽ 1


የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## ሳሞራ የኑስ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያው ባለሙሉ ማእረግ ጄኔራል እንደተባለ እና ሃውልት እንደተገነባለት ተዘገበ

በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ የወያኔ አገዛዝ ዘረኛ ፖሊሲ ዋና አስፈጻሚ የሆነው ሳሞራ የኑስ በኢትዮጵያ የመከላከያ ታሪክ ውስጥ ያለፉ ብዙ ጀግኖች አግኝተው የማያውቁት ማእረግ እንደተሰጠው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት - ኢሳት - ዘግቧል።

ሳሞራ የኑስ በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ባለሙሉ ማእረግ ጀኔራል ተብሎ መሰየሙን እና ሃውልት ተገንብቶለት በብሔራዊ ሙዚየም መቀመጡን ዘገባው አመልክቷል። በሃውልቱ እግርጌ የተቀመጠው የህይወት ታሪክ፣ ሳሞራ የወያኔን የትጥቅ ትግል የተቀላቀለው አስራ አንደኛ ክፍል ጨርሶ እንደሆነ ከገለጸ በኋላ እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ኦፕን ዩኒቨርሲቲ የማስትሬት ዲግሪውን ማግኘቱን እንደሚናገር ታውቋል። ሳሞራ አስራ ሁለተኛ ክፍልን እና የመጀመሪያ ዲግሪውን የት እንዳገኘ የህይወት ታሪኩ እንደማይናገር ኢሳት ጠቁሟል።

የቀድሞው የወያኔ የፕሬስ መምሪያ ሃላፊ ጋዜጠኛ ተስፋዬ ገብረአብ፥ በርካታ የወያኔ ባለስልጣናት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መልስ አስቀድሞ ተሰጥቷቸው አስራ ሁለተኛ ክፍልን እንደጨረሱ ማጋለጡ ይታወሳል። “የውጭ ጉዳይ ነገር” በሚል ርእስ የግንቦት 7 ምንጭ ከዚህ ቀደም ባወጣው ጽሁፍ ደግሞ የወያኔ ባለስልጣናት የአገሪቱ ህግ በሚጠይቀው መሰረት የመጀመሪያ ዲግሪ ሳይዙ በህዝብ ገንዘብ ከውጭ ሃገር የተገዛ የሁለተኛ ዲግሪ ማስረጃ እያመጡ ህገ-ወጥ እድገት እና የደሞዝ ጭማሪ እንደሚሰጣቸው አጋልጧል።

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ባስመሰከሩት የግል ችሎታ ከፍተኛ ትምህርት የቀሰሙና ትላልቅ አለማቀፍ እና አገራዊ ጦርነቶችን የመሩ ጄኔራሎች፣ ሳሞራ የኑስ አሁን በትግራዋይነቱ ያገኘው ማእረግ አልተሰጣቸውም።

## በአስመጪነት ንግድ የተሰማሩ ዜጎች ከወያኔ አባላት በሚደርስባቸው ህገ-ወጥ ውድድር እየተገፉ መሆኑ ታወቀ

ግብር የማይከፍሉ የወያኔ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች ህግ አክብረው የሚሰሩ አስመጪ ነጋዴዎችን ከገበያው እየገፉ መሆናቸውን የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ ዘግቧል።

በርካታ አስመጪ ነጋዴዎች ድርጅቶቻቸው አትራፊነታቸውን በማጣታቸው የንግድ ዘርፋቸውን ለመለወጥ እየተገደዱ ነው ያለው ዘጋቢ፤ እንዲከፍሉ የሚጠየቁት የግብር መጠን ሆን ብሎ ከመጠን ያለፈ ስለመሆኑ ምሬታቸውን እንዳሰሙት ገልጿል።

ለደህንነታቸው ሲሉ የድርጅቶቻቸው ስሞች እንዳይጠቀሱ የፈለጉት ነጋዴዎች፤ የገጠማቸው ችግር የፈተጠረው የተሰማሩበት ንግድ ተጠቃሚዎች አጥቶ ሳይሆን የገዢው ቡድን አባል የሆኑ ነጋዴዎች በዝቅተኛ ግብር ወይም በነጻ እያስመጡ በዝቅተኛ ዋጋ ለመሸጥ በመቻላቸው ነው ብለዋል። ይህ ሁኔታም ባሉበት የንግድ ዘርፍ ለመወዳደር እንዳላስቻላቸው እና ከገበያው መገፋታቸውን አስረድተዋል።

## የብአዴንን ልደት ለማክበር በአዲስ አበባ የተጠራው የጽዳት ዘመቻ በተሳትፎ እጥረት ከሸፈ

ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ - ብአዴን - የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ፓርቲ የልደት ቀኑን ለማክበር በአዲስ አበባ የጠራው የጽዳት ዘመቻ የከተማውን ህዝብ ቀልብ ለመሳብ ባለመቻሉ ሳይሳካ መቅረቱን ከመዲናይቱ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

ላለፉት ሃያ አመታት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የአማራን ህዝብ ረግጦ እንዲገዛ ሲያቀናጅ የቆየው እና እንደበረከት ስምኦን፣ አዲሱ ለገሰ እና ተፈራ ዋልዋ ባሉ በህዝብ የተጠሉ ግለሰቦች የሚመራው ድርጅት እወክለዋለሁ በሚለው የአማራ ህዝብ ዘንድ በንቀት እንደሚታይ ይታወቃል።

ብአዴን በአዲስ አበባ በጠራው የጽዳት ዘመቻ ላይ አሳፋሪ የሆነ የሰው ቁጥር መገኘቱ፣ የወያኔ አገዛዝ እና ተለጣፊ ድርጅቶቹ ለመልካም አላማ እንኳ ህዝብ ማሰባሰብ እንዳቃታቸው ጉልህ ማስረጃ ነው ሲሉ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል።

## አትሌት ሃይሌ ገብረስላሴ ከወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ጫና እየተደረገበት ነው የተባለውን አስተባበለ ተባለ

ዝነኛው አትሌት ሃይሌ ገብረስላሴ ከዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ጫና እየደረሰበት ነው ሲል ታዋቂው ኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጣ የሯጩን ማኔጀር ጠቅሶ ዘግቧል። ከሁለት ቀናት በኋላ ግን አትሌቱም ማናጀሩም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው ዘገባውን አስተባብለውታል።

ሃይሌ ገብረስላሴ ኖቬምበር 7 ቀን የተካሄደውን የኒው ዮርክ ከተማ ማራቶን በጉልበት ህመም ሰበብ ማቋረጡ እና ከእስፖርት አለም ጡረታ መውጣቱን አውጆ እንደነበር ይታወሳል። ባለፈው ሰኞ ግን በቤተሰብ እና ጓደኞች ጉትጎታ ምክንያት ውሳኔውን ማጠፉን አረጋግጧል።

የአትሌቱ ማኔጀር የሆነው ኔዘርላንዳዊው ጆስ ሄርመንስ፥ ሃይሌ በወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ጫና እየደረሰበት እንዳለ ለኒው ዮርክ ታይምስ ተናግሯል። የሃይሌ ስልክ መጠለፉን እና ማስፈራሪያ እየተደረገበት እንዳለም አስረድቷል። ሚስተር ሄርመንስ ጨምሮም፥ ሯጩ የኒው ዮርክ ማራቶንን አቋርጦ መውጣቱን ተከትሎ ያስተላለፈው የጡረታ አዋጅ ከዚህ ሁሉ ጫና የተነሳ ያደረበት የስሜት መረበሽ ውጤት ነው ብሏል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ፍትህ የተነፈጉ ኢትዮጵያውያን በወያኔ ሹመኞች ላይ ጥቃት መፈጸም መጀመራቸውን ዘገባዎች አመለከቱ

የሱሉልታ ከተማ ነዋሪዎች ባለፈው ሳምንት በከተማቸው የወያኔ ሹመኛ ላይ የጥቃት እርምጃ ወስደዋል ሲል የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት - ኢሳት - ዘግቧል።

የኢሳት ዘገባ እንዳመለከተው፥ መሬታቸው በህገ-ወጥ መንገድ የተቀማባቸው ነዋሪዎች የከተማዋ ከንቲባ ከስልጣን መውረዱን ሲሰሙ፣ በሱና በተባባሪው ላይ ድብደባ ፈጽመዋል። ከባለስልጣኑ መሬት የወሰዱ ባለሃብቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ጥቃት እንደተፈጸመባቸው ታውቋል። የከተማው ፖሊስ ጥቃቱን ተከትሎ የተነሳውን ረብሻ ለመቆጣጠር ባለመቻሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ወደ አካባቢው መሄዳቸውንም የኢሳት ዘገባ ገልጿል።

በወያኔ አገዛዝ ሹመኞች ላይ በሱሉልታ የተፈጸመው ጥቃት ከመሬት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ይሁን እንጂ፤ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ ዜጎች መብታቸውን የማስከበሩን ጉዳይ ወደገዛ እጃቸው መውሰዳቸውን መረጃዎች እያመላከቱ ነው። ከዚህ በፊት ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ጉኢሽ የተባለው የአላማጣ ከተማ ከንቲባ በተመሳሳይ ሁኔታ በነዋሪዎች ድብደባ ደርሶበታል። በህዝቡ ላይ የሚያደርሰውን ግፍ ካላቆመ ተጨማሪ ቅጣት እንደሚደርስበት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት መለቀቁንም የደረሰ መረጃ ጠቁሟል።

## በኢትዮጵያ የተፈጸሙ የዘር ማጥፋትና የጦር ወንጀሎችን እንዲያጣራ ለተባበሩት መንግስታት የሚደረጉ ጥሪዎች ጨምረዋል

“የኢትዮጵያ ሴቶች የሰብአዊ መብት ጥምረት” የተባለው ድርጅት ባለፈው ሳምንት በላከው ደብዳቤ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽነር ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጽማቸውን ከፍተኛ ወንጀሎች እንዲያጣሩ ጥሪ እንዳደረገ ለማወቅ ተችሏል።

ጄኖሳይድ ዋች የተባለው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት በ2001 አመተ ምህረት ተመሳሳይ ደብዳቤ ለከፍተኛ ኮሚሽነሯ ዳኛ ናቫነተም ፒለይ መላኩ ይታወሳል። “የኢትዮጵያ ሴቶች የሰብአዊ መብት ጥምረት” በደብዳቤው፥ ኮሚሽነሯ ልዩ አጣሪ መድበው በኢትዮጵያ የሚካሄደውን የሰብአዊ መብት ረገጣ እንዲያስመረምሩ ጠይቋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የሚሰማ ጆሮ ያለው፤ ይስማ !!!

"ጄኖሳይድ ዋች" ወደ ዘር ማጥፋትና ጅምላ ፍጅት የሚያመሩ ሁኔታዎችን በመከታተል ለመከላከል፤ የዘር ማጥፋትና የጅምላ ፍጅት ከተፈፀመም የወንጀሉ ፈፃሚዎችን ወደ ህግ ለማቅረብ የተቋቋመ ዓለም ዓቀፍ ተሚጋች ድርጅት ነው። ይህ ድርጅት መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ተቋማት የዘር ማጥፋትና የጅምላ ግድያዎችን እንዲከላከሉ፤ ወንጀለኞች ተከሰው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ወትውቷል፤ እየወተወተም ነው። ጄኖሳይድ ዋች የዘር ፍጅትና የጅምላ ጭፍጨፋዎችን በመቃወም የሚደረጉ ህዝባዊ ንቅናቄዎችን በግንባር ቀደምትነት መርቷል፤ አሁንም በመምራት ላይ ይገኛል። ከዚህ ቀደም በካምቦዲያ፣ በዩጎዝላቪያ፣ በሩዋንዳ፣ በካሜሮን፣ በሱዳን እና ሌሎች በርካታ አገራት ውስጥ የደረሱ የዘር ፍጅቶችን መርምሮ ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ ለማድርግ የቻለ፤ በሥራው ውጤትም ዓለም ዓቀፍ ከበሬታን ያገኘ ድርጅት ነው።

ይህ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ በጋምቤላ፣ በኦጋዴን፣ በሃዋሳ፣ በአዲስ አበባ እና ሌሎችም አካባቢዎች የተደረጉ የዘር ፍጅቶችና ኢሰብዓዊ ግድያዎችን በመመርመር፤ በሶማሊያ ውስጥ በሰላማዊ ዜጋ ላይ የተፈፀሙ የጦር ወንጀሎችና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በመዘርዘር የዚህ ሁሉ ግንባር ቀደም አስተባባሪ የሆነው አረመኔው መለስ ዜናዊ ሄይግ በሚገኘው ዓለም ዓቀፍ ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶበት ጉዳዩ በህግ እንዲታይ ባለፈው ዓመት የተባበሩት መንግሥታትን ጠይቆ ጉዳዩን እየተከታተለ ይገኛል።

በጥቅምት ወር 1998 ዓም በግፍ የተጨፈጨፉ ወገኖቻችንን ለማስታወስ በቅርቡ በዋሽንግተን ዲሲ በተጠራው የሰማእታት መታሰቢያ ዝግጅት የዚህ ታዋቂ ድርጅት ፕሬዚደንት የሆኑት ዶ/ር ግሪጎሪ ስታንተን በክብር እንግድነት ተገኝተው ነበር።

ዶ/ር ስታንተን በዚህ ዝግጅት ያደረጉትን ንግግር ጆሮ ያለው ሁሉ ሊሰማው፤ አዕምሮ ያለው ሁሉ በአንክሮ ሊያጤነው የሚገባ ነው። ዶ/ር ስታንተን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ "የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ" ብለውታል። በዚሁ ንግግራቸው "የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ የመለስ አገዛዝ መውደቁ የማይቀር ነገር ነው" ካሉ በኋላ ለመለስ ወንጀሎች የትግራይ ህዝብ ዋጋ ከፋይ ሊሆን የሚችል መሆኑ እያስጨነቃቸው መሆኑን ገልፀዋል። ለዚህ ግምትም መነሻ የሆኗቸውን በቅርብ ጊዜ የተፈፀሙ የዘር ማጥፋት ፍጅቶችን በምሳሌነት አንስተዋል። በሩዋንዳ፣ ካምቦዲያ፣ እና ሱዳን የደረሱት የዘር ፍጅቶች መሠረታቸው የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ መሆኑን አብራርተዋል። ኢትዮጵያ ላይ ያጠላውን አደጋ ለመወጣት የነፃነት ኃይሎች ተባብረው መቆም እንዳለባቸው መክረዋል። በተለይም የትግራይ ልሂቃን ላይ የወደቀው ኃላፊነት ከፍተኛ እንደሆነ አጽንዖት ሰጥተውበታል።

ከዶ/ር ስታንስተን ንግግር ውስጥ ሁለት ዓበይት ነጥቦች ላይ ማትኮር እንፈልጋለን

1. "የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ" ምን ማለት ነው? ውጤቱስ ምንድነው?

   የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ በአንድ አገር ውስጥ የሚገኝ አንድ የኅብረተሰብ ክፍል ከራሱ ወገን ውጭ የሆኑትን የአገሪቱን ዜጎች ወሮ እንደያዘው አገር ህዝብ አዋርዶ የሚገዛበት ሥርዓት ነው። የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ መሠረቱ ዘውግ፣ ቋንቋ ወይም ሃይማኖት ሊሆን ይችላል። በብዙ ሁኔታዎች የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ እና የባዕድ ቅኝ አገዛዝ ተመሳሳይ ናቸው። በሁለቱም ውስጥ የሚደረጉ የነፃነት ትግሎችም ተመሳሳይ ባህርይ አላቸው። ሁለቱም ዓላማቸው ህዝብንና አገርን ማዳን ነው። የአገር ውስጥ ቅኘ ተገዢዎች የራሷ ሰንደቅ ዓላማ ባላት አገር ውስጥ መሆናቸው ትግላቸውን ያከብደው እንደሆን እንጂ የሚደርስባቸውን ጥቃት አያቀለውም።

2. በዚህ ጉዳይ ላይ የትግራይ ምሁራን ሚና ምን መሆን ይኖርበታል?

   ዶ/ር ስታንተን እንደገለፁት፤ እኛም እንደምናውቀው የመለስ አገዛዝ የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ነው። ይህ አገዛዝ መሠረቱ ያደረገው ትግራይን ነው። በግልጽ ተነገረም አልተነገረ የሥርዓቱ ግብ የትግራይን የበላይነት እና የሌሎች ኢትዮጵያዊያንን የበታችነት ማረጋገጥ ነው። የትግራዩ ጉጅሌ እስካሁን ብዙ ተሳክቶለታል። እንደማንኛውም ቅኝ ገዢ ቁልፍ ቦታዎችን በጉጅሌው አባላት እየተቆጣጠረ በወረራ የያዘዘው ግዛት ከዚያው አካባቢ በተገኙ ባንዳ ምስለኔዎች ተከልሎ ይገዛል። ዶ/ር ስታንተንን ያሰጋቸው ይህ ሥርዓት የተናጋ እለት ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ እኛንም በእጅጉ ያሳስበናል።

የትግራዩ ጉጅሌ ሥልጣን ከእጁ የወጣ እለት በቅኝ አገዛዝ የተማረረው ህዝብ የሚወስደውን እርምጃ መቆጣጠር ያዳግት ይሆናል። የዘር ፓለቲካ መለስ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ መንግሥታዊ ፓሊሲ ሆኖ ሲሰራበት የቆየ በመሆኑ ሊያመጣ የሚችለው መዘዝ ቀላል እንደማይሆን መገመት ብልህነት ነው። በዚህ መዘዝ ደግሞ ክፉኛ ተጠቂ የሚሆነው የትግራይ ህዝብ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንፃራዊ መልኩ የትግራይ ምሁራን ከወያኔ መስመር እየወጡ መሆኑ በጎ ጅምር ነው። ቀድሞ የመለስ ዜናዊ አማካሪ የነበሩት ፕሮፌሰር ተኮላ ሃጎስ፤ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያ እና በህዝቧ ላይ የሚፈጽማቸውን ግፎች ያለ ትግራውያን እርዳታ ሊያደርገው ባልቻለ ነበር ሲሉ ከሣምንታት በፊት ለንባብ ባበቁት ጽሁፍ መግለፃቸው እና የትግራይ ተወላጆች የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያደርገውን ትግል እንዲቀላቀሉ ማበረታታቸው መልካም ነገር ነው።

ሆኖም ግን ከትግራይ ምሁራን ከዚህ በላይ እንጠብቃለን። ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ማስቀረት የምንችለው አሁን ነው። የትግራይ ህዝብ ጥቅም በዘላቂነት የሚከበረው የመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት ሲረጋገጥ መሆኑ ለሁሉም የትግራይ ምሁራን ግልጽ ሊሆን ይገባል እንላለን። ስለሆነም ለራሳችሁ፣ ለትግራይ ህዝብ፣ ለትግራይ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ እና ለኢትዮጵያ ደህነት ስትሉ የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝን ለማጥፋት በምናደርገው ትግል ከሌሎች ወገኖቻችሁ ጎን እንድትሰለፉ ጥሪዓችንን እናቀርባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

## በዳላስ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የዘረኛው አገዛዝ ተወካዮች ያዘጋጁትን ስብሰባ አስተጓጎሉ

የሎስ አንጀለሱ የወያኔ ቆንስላ ሹመኛ ታዬ አስቀስላሴ በዳላስ ላሉ ኢትዮጵያውያን ስለ እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተብዬው ገለጻ ለመስጠት የተገኘበት ስብሰባ በአካባቢው ባሉ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ተቃውሞ ተስተጓጉሏል።

ሰዎች እሱን ሊሰሙ የተሰበሰቡ የመሰለው ታዬ በፈገግታ ሲፈካ፣ ንግግሩን ሳይጀምር የቀደመው አንድ ኢትዮጵያዊ ተሰብሳቢዎቹ በድህረ-ምርጫ 97 ለወደቁት ሰማእታት የህሊና ጸሎት በማድረግ ስብሰባውን እንዲጀምሩ ጠይቋል። ቀጥሎም በስብሰባው አዳራሽ ከተገኙት ውስጥ አብዛኞቹ አስቀድመው የተጠራሩ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው፣ ጥሪውን በመቀበል ተነስተው ቆመዋል።

በወቅቱ ከመድረኩ አካባቢ የሚመጡ ድምጾች፥ "የምን ሰማእታት?" እያሉ ይጠይቁ ነበር፤ ከተሰብሳቢዎቹ አንዱም "ለሁሉም ሰማእታት፣ ደርግ ለገደላቸውም ይሁን ለሁሉም" ብሎ ለማብራራት ቢሞክርም፤ በጉዳዩ ያልተደሰቱ ጥቂት የዘረኛው አገዛዝ ደጋፊዎች አተካራ ፈጥረዋል። መድረክ ላይ ቆሞ እድል እንዲሰጠው ሲማጸን የነበረው ታዬ፤ በተሳታፊዎቹ ከቁብ ባለመቆጠሩ ቀጥሎ የተነሳውን ረብሻ ለማስቆም አልቻለም።

ታዬ አስቀስላሴ የወያኔ ላንቲካ ወይም የምልክት ሹመኛ ነው ያሉን አንድ የዝግጅት ክፍላችን ምንጭ፤ በሎስ አንጀለስ በሚገኘው ቆንስላ፣ እውነተኛው ባለስልጣን ከሱ በስተጀርባ የተቀመጠው ተክሉ ሃብተወልድ ነው ብለዋል። እኒሁ ምንጭ፥ ግለሰቡ ዘረኛውን አገዛዝ በመወከል ራሱን የሚያዋርድበት ምክንያት ጥቅም እንደሆነ በመግለጽ፤ በ1997 ምርጫ ማግስት ተቃዋሚዎች ስልጣን የሚረከቡ መስሎት ለአንድ የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ቡድኖች አመራር አባል ስልክ ደውሎ "እንዴት ልርዳችሁ?" ብሎ መጠየቁን ለጉዳዩ ቅርበት ካላቸው ግለሰብ እንደሰሙ ጠቅሰዋል።

## ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ በደቡብ ኮሪያ ተቃውሞ ገጠመው

ቡድን ሃያ የሚባለው የሃያላን መንግስታት ስብሰባ ሲካሄድ የአፍሪካ አገራትን ወክሎ የተገኘው ዘረኛ አምባገነን መለስ ዜናዊ በደቡብ ኮሪያ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተቃውሞ እንደገጠመው ከስፍራው የደረሰን መረጃ አሳውቋል።

የተቃውሞ ሰልፉ አስተባባሪዎች በለቀቁት መግለጫ እንዳሳወቁት፣ አገዛዙ ዝግጅታቸውን ለማጨናገፍ ሲያደርግ የቆየው ሙከራም ከሽፏል። የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያውያን የተቃውሞ ሰልፉን በመሳተፍ ፈንታ ከመለስ ዜናዊ ጋር ምሳ እንዲበሉ ሲያባብል የቆየ ሲሆን፤ አብዛኛው ስደተኛ ግብዣውን ውድቅ አድርጎታል።

ከተለያዩ የደቡብ ኮሪያ ክፍሎች ወደ ሴኡል ከተማ ለሰልፍ የወጡት ኢትዮጵያውያን፥ ሃያላን መንግስታቱ ጸረ-ሰላም እና ጸረ-ሰብአዊ መብት ለሆነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ድጋፍ እንዳይሰጡ ጠይቀዋል። አስከፊውን ስርአት ለመጣል በመላው አለም ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ጋር በቁርጠኝነት ለመታገል ቃልም እንደገቡም ታውቋል።

የዝግጅቱ አስተባባሪዎች፥ በዚሁ አጋጣሚ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በተቀናጀ ሁኔታ ለመታገል እንዲነሱ እና ልሂቃንም ልዩነቶቻቸውን አጥብበው ትግሉን ለመምራት እንዲነሱ ጥሪ አቅርበዋል።

## በኢትዮጵያ የተፈጸሙ የዘር ማጥፋትና የጦር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ስለሚፈጽማቸው የሰብአዊ መብት ረገጣዎች ገለልተኛ እና የተከበሩ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ቢያሳውቁ እና ቢመዘገቡም፤ እስካሁን ወንጀለኞቹን ለፍርድ ለማቅረብ የተካሄደው እንቅስቃሴ አለመኖሩን ጠቁሟል። በዚህም ምክንያት ከወንጀሎቹ በስተጀርባ ያሉት ግለሰቦች በማናለብኝነት ግፍ መፈጸም መቀጠላቸውን አስረድቷል።

ደብዳቤው፥ ከአምስት አመታት በፊት በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትእዛዝ ንጹሃን ዜጎችን ለመጨፍጨፍ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ በተለቀቀው የአጋዚ ጦር በልጆቻቸው ፊት የተገደሉትን የስምንት ልጆች እናት ወ/ሮ እቴነሽ ይማምን ጉዳይ እንደ አንድ ምሳሌ ጠቅሷል።

ጥምረቱ፥ ኮሚሽነሯ የኢትዮጵያን ሴቶች ስሞታ ተቀብለው ልዩ አጣሪ እንዲሾሙ ተማጽኖውን አቅርቧል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ወደፊት መውደቅ!

**ዶ/ር ታደሰ ብሩ - እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 8 ቀን 2010 በለንደን የሰማዕታት መታሰቢያ ዝግጅት ላይ ያደረጉት ንግግር**

**ክቡራትና ክቡራን!!!**

በጥቅምት 1998 ዓም በግፍ የተጨፈጨፉ ወገኖቻችንን ለመዘከር በተጠራው በዚህ ስብሰባ ላይ እንድናገር እድል ስለተሰጠኝ ምስጋና አቀርባለሁ። የሰኔ 97 እና ጥቅምት 98 ጭፍጨፋዎች እና አፈናዎች ሲፈፀሙ በቦታው የነበርኩ፤ በአፈናውም በቀጥታም በተዘዋዋሪም የተነካሁ በመሆኔ መራር ትዝታዎቼ ህያው ናቸው።

ሚያዝያ 30 1997 የነበረው የአንድነትና የደስታ ስሜት፤ ግንቦት 7 ቀን የነበረው ልበ-ሙሉነትና ተስፋ በሰኔ ወር ላይ ተነቅንቆ ጥቅምት ወር ላይ ሲደረመስ ማየት ልብን ይሰብራል።

ህፃናት ሲገደሉ፤ እናቶች ሲያለቅሱ፤ ወጣቶች ሲታፈሱ እያዩ ምንም አለማድረግ ራሱን የቻለ ሰቀቃ ነው። ለአሜሪካና እንግሊዝ ኤምባሲዎች የጎረፈው የድረሱልን እና የእወቁልን ጥሪዎች ብዛት እና የእነሱ ዝምታ ሲጤን “እውን የነፃነትና ዲሞክራሲ አጋር ማነው?” ያስብላል።

አዎ በጥቅምት 98 ህፃናት፣ ወጣቶችና አረጋዊያን በግፍ ተጨፍጭፈዋል። በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የአካል ጉዳተኞች ሆነዋል። በመቶ ሺህዎች የሚገመት ህዝብ ተደብድቧል፣ ተተፍቶበታል፣ ተሰድቧል፣ ተዋርዷል።

ከዚህ ሁሉ ጋርም ለዓመታት የገነባነውን መሪዎቻችንን የመምረጥና የመሻር ህልም ቅዠት ተደርጎብናል። “እያንዳንዷ ድምፅ ዋጋ አላት!” እንዳላልን ሁሉ ኮሮጆ ሙሉ ድምፅ ዋጋ ሲያጣ እያየን መከላከል አቅቶናል።

የጥቅምትን ፍጅት ተከትለው የመጡ ኩነቶች እጅግ አሳዛኝ እና ተስፋ አስቆራጭ ነበሩ። አንዳንዶቹ ከማሳዘን ብዛት አስቂኝ ነበሩ።

ለምሳሌ የወያኔ ሰላዮች “እኛ ሞተን የገነባነውን ሥርዓት እናንተ ማኪያቶ እየጠጣችሁት ልትንዱ እንዴት ከጀላችሁ?” እያሉ በግልጽ የሚናገሩበት ጊዜ ነበር። እኔ በግል በተደጋጋሚ እንዲህ ተብዬ “እውነት እንዴት ሞኝ ብሆን ነው የሞቱበትን ሥልጣን በካርድ ይለቃሉ ብዬ ያመንኩት?” ብዬ በራሴ ላይ ስቄዓለሁ፤ ራሴን ታዝቤዓለሁ።

ቀድሞ በየስብሰባው አዳራሽ ከኔወዲያ ለዲሞክራሲ መፋለም ላሳር ሲል የነበረ ወዳጃችሁ ከወያኔ ጋር ሲሞዳሞድ ስታነገኙት፤ ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ሲረክሱባችሁ ማየት ተስፋ አስቆራጭ ነው።

ስለ ሰኔና ጥቅምት ፍጅቶች እስካሁን ብዙ ተብሏል። ያም ሆኖ ግን ያልተነገረው ከተገረው በእጅጉ ይበልጣል። በዚህም ምክንያት ወደዚህ ርዕስ ደጋግመን መመለሳችን የሚቀር አይመስለኝም። ያኔ ስለተፈጸሙ የጭካኔ ተግባራት መዘከር ጥሩ ነው። ዝክሮቻችን መቋጫ ከሌላቸው ግን ሰማዕታቱንም የሚያስደስት አይመስለኝም።

ለመሆኑ ጥቅምት 1998 የሆነው ምንድነው? ለምንድነው ፍጹም በሆነ ጭካኔ የተደበደብነው፣ የተገረፍነው፣ የተጋዝነው እና የተገደለነው? ምን ስላደረግን ነው ያ ሁሉ ግፍ የተፈፀመብን?

ለእነዚህ ጥያቄዎች የጋራ መልስ ኖሮን ቢሆን ኖሮ ከዚያ ወዲህ የተፈጠሩ ብዙዎቹን ልዮነቶች ባልኖሩም ነበር:: እንደኔ እምነት በጥቅምት 1998 በጭካኔ የተመታው ያዋጣል ብለን ተስፋ ያደረግንበት የትግል ስትራቴጂ ነው። የሰላም እርግብን ለመግደል እርግብ የመሳሰሉ ህፃናትን ገደለ። መለስ በምን ዓይነት መንገድ ሥልጣን በፈቃዱ በእጁ እንዲወጣ እንደማይፈቅድ ከህዝብ ተነጥሎ ሲቀለብ የቆየን ጦርን ከተማ ውስጥ በማሰማራት እምን ደረስ መሄድ እንደሚችል አሳየን። በጥቅምትና ተከታዮቹ ጥቂት ወራት አገሪቱ ሙሉ በሙሉ የምትመራው በጦር ሠራዊትና በሰላዮች ብቻ ነበር። እነዚህ ደግሞ የአንድ ጎጥ ሰዎች ናቸው። ባጭሩ የጥቅምት ጅምላ ጭፍጨፋ መልዕክት “ሥልጣኔን ከምለቅ አገሪቷን ከነህዝቧ ባቃጥል እመርጣለሁ” ነው። ጥቅምት ላይ ስለሆነው ነገር ግልጽ ያልሆነልን ጉዳዩ ውስብስብ ሆኖ አይደለም። “ወያኔ በሚቆጣጠረው ምርጫ ወያኔን ማሸነፍ የማይቻል ከሆነ ምንድነው መደረግ ያለበት?” የሚለው ጥያቄ ምላሽ እረፍት የሚነሳ መሆኑ ነው። የጥያቄው ቀጥታ ምላሽ ግባችንን አሊያም ስልታችንን መቀየር አለብን የሚል ነው። ሁለቱም አማራጮች ምቾት የሚሰጡ አይደሉም።

እንዲህ መንፈሴ በተረበሸበት እና የተስፋ መቁረጥ ስሜት እየተፈታተነኝ በነበረበት ወቅት ነበር የጆን ማክስዌል **“ወደፊት መውደቅ፤ ስህተቶችን ወደስኬት መረማመጃነት መቀየር /Failing Forward: Turning mistakes into stepping stones for success/** የተሰኘውን መጽሃፍ ያነበብኩት። ይህ መጽሃፍ ስለ ውድቀት /failure/ የነበረኝን አስተያየት ሞርዶታል ብዬ አምናለሁ። በተጨማሪም እኛ ኢትዮጵያዊያን ከስህተቶቻችን የመማር ችግር ያለብን መሆኑ ምንኛ እንደጎዳን እንዳሰላስል ረድቶኛል። ከጥቂት ወራት በፊት “ወደፊት መራመድ እንዴት አቃተን? ለወደፊቱስ ምን ማድረግ እንችላለን?” በሚል ርዕስ ባቀረብኩት አጭር ጽሁፍ ወደፊ ት እንዳንራመድ ካሰናከሉን ችግሮቻችን አንዱ ከውድቀቶች መማር አለመቻላችን ነው የሚል ሃሳብ አቅርቤ ነበር። ያኔ እንደገለጽኩት ወደፊት መውደቅ ከማዝገም እጅግ ..... እጅግ ... እጅግ ይሻላል። ከማይረባ ስኬት ደግሞ ዋጋ ላለው ጉዳይ ታልሞ ያልተሳካ ሙከራ በእጅጉ ይሻላል።

ከዚህ አንፃር ሲታይ የ97ቱ በምርጫ ካርድ መንግሥትን የማውረድ ሙከራ ባይሳካም ሙከራው ብቻውን ከፍተኛ ዋጋ ያለው ታሪካዊ ክስተት ነው። ድህረ ምርጫ 97 ኢትዮጵያ ከዚያ በፊት ከነበረችው ኢትዮጵያ በብዙ ነገሮች ትለያለች። ስለሆነም የሰማዕቶቻችን መስዋዕትነት መና አልቀረም።

እርግጥ ነው በ1998 ውድቀት ደርሶብናል። መውደቅ በራሱ መጥፎ ነገር አይደለም። ውድቀትን በአጠቃላይ በተመለከተ የሚከተሉትን ሰባት ነገሮች ማለት ይቻላል።

1. ውድቀትን ለሁልጊዜው ማስቀረት አይቻልም። መውደቅ የማይቀር ነገር ነው፤
2. ውድቀት ክስተት አይደለም። እንደ ስኬት ሁሉ ውድቀትም የሥራ ሂደት ውጤት ነው፤
3. ውድቀት ግዑዝ ነገር አይደለም። እኛ ነን ውድቀትን ከግዑዝ ነገር ጋር የምናያይዘው፤
4. ውድቀት ጠላታችን መሆን የለበትም። እንዲያውም መድከማችንን የሚነግረን ወዳጃችን ነው፤
5. ውድቀት የማይጠገን ወይም የማይመለስ ነገር አይደለም፤
6. መውደቅ አሳፋሪም አስነዋሪም ነገር አይደለም። እያንዳንዱን ውድቀት ወደ ስኬት የሚያመራ መረማመጃ ማድረግ ይቻላል፤
7. ውድቀት የጉዞ መጨረሻ አይደለም። እንዲያውም ወደ ስኬት ለሚደረግ ጉዞ የሚከፈል ዋጋ ነው።

በ98 ወድቀናል፤ ይሁን እንጂ ሁላችንም ወደ አንድ አቅጣጫ አልወደቅንም። ከፊሎች ወደፊት ወድቀው ተነስተው በአዲስ መንፈስ መንገዳቸውን ቀጥለዋል። ሌሎች ደግሞ ወደኋላ ወድቀው እየዳከሩ ነው። እንደማክስዌል ገለፃ

1. ወደ ኋላ መውደቅ ፍርሃትን ያነግሳል። ወደኋላ የወደቀ ሰው በድጋሚ ላለመውደቅ አለመነሳትን ሊመርጥ ይችላል። ቢነሳም እንኳም እርምጃው ፍርሃት እና ጥንቃቄ የበዛበት በመሆኑ ከመውደቁ በፊት በነበረው ጥንካሬና እልህ መቀጠል አይችልም፤
2. ወደ ኋላ መውደቅ ስንፍናን ያበረታታል። ጊዜን ይገላል፤ ምርታማነት ይቀንሳል፤ አዳዲስ ሃሳቦችን የማፍለቅንም ሆነ የመቀበል ችሎታን ያሽመደምዳል፤
3. ወደኋላ መውደቅ ግብን በጣም ስለሚያርቅ ተስፋ ያስቆርጣል። ይህ ደግሞ ከፍርሃት ጋር ሲጣመር ቀድሞ በጣም ውጤታማ የነበሩ ሰዎችን እንኳን ሳይቀር ሽባ ሊያደርግ ይችላል።

በአንፃሩ ወደፊት የወደቀ ሰው ተነስቶ በራሱ ላይ ስቆ አቧራውን አራግፎ መንገድ እየመረጠ ይሄዳል። ወደፊት ወድቆ የተነሳ ሰው ጭራሹን ካልወደቀ ሰው ይሻላል። ይህ ማለት ግን ወድቆ የተነሳ ሰው የሚመርጠው መንገድ አደጋ የሌለው ነው ማለት አይደለም። አደጋ የሌለው መንገድ የለም። እንዲያውም አዲሱ መንገድ ከቀድሞው የባሰ አደጋ ያለው ያለው ሊሆንም ይችላል። ወደፊት ወድቆ የተነሳ ሰው ወድቆ ጠንክሮ መነሳት ለምዷልና ዳግም የመውደቅ ፍርሃት የለበትም።

ከሰኔና ጥቅምት ጭፍጨፋዎችና አፈናዎች በተገቢው ሁኔታዎች አለመማራችን ለተዘበራረቀ አወዳደቃችን ምክንያት ሆኗል ብዬ አምናለሁ። ጊዜ ወስደን ልንመረምራቸው የሚገቡ በርካታ ጥያቄዎች ነበሩ፤ አሁንም አሉ

1. የ97 እና 98 ን ህዝባዊ መነሳሳት በተለየ ሁኔታ መምራት ይቻል ነበር ወይ?
2. ለምንድነው ወያኔ የ98ቱን ሰላማዊ መነሳሳትን በፍጹም ጭካኔ የደፈጠጠው?
3. ምንድነው የዚያ ጭካኔ ምንጭ? እንደምን ያለ ቅስቀሳ ነው ወታደሮቹ ህፃናት ግንባር ላይ እንዲተኩሱ ያስቻላቸው?

ማነው የትግላችን አጋር? ለምንድነው አሜሪካ እና እንግሊዝ የሰሙትን እንዳልሰሙ፤ ያዩትን እንዳላዩ የሚሆኑት? ከዚህ ውጭ መሆን ይችሉ ነበር ወይ? ጥያቄዎቹ በርካታ ናቸው። አንዳንድ ሰዎች እነዚህን መሰል ጥያቄዎች ማንሳትና ማውጠንጠን ባለመፈለጋቸው ለወደኋላ መውደቅ አጋለጣቸው። በ1998 በርካታ ዜጎቻችን ውድ ህይወታቸውን አጥተዋል። የዚያኑ ያህል ደግሞ ጥቂት የማይባሉ ወገኖቻችን ስነ-ልቦናዊ ሞት ሞተዋል።

**ንግግሬን ልቋጭ**

በ1998 ወገኖቻችን በግፍ ተገድለውብናል። በርካታ ዜጎች ተደብድበዋል፣ተገርፈዋል። በ1997 ተስፋ ሰጪ የነበረው የትግል ስልት በ1998 ሳንካ ደርሶበታል። “ከዚህ ሳንካ ምን ተማርን?” የሚለው ነገር የወደፊቷን ኢትዮጵያ እድል ይወስናል:: ከውድቀታችን ተምረን መስመራችንን አስተካክለን ከሆነ እሰየው!!! ሰማዕታቱን የምንዘክራቸው እዚያው እወደቅንበት ቦታ ላይ ሆነን ከሆነ ግን ባንዘክራቸው ይሻላል።

ወገኖቼ መውደቅ ያለ ነገር ነው። ወደፊትም ብዙ መውደቆች ሊያጋጥሙን ይችላሉ። አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ወደፊት ለመውደቅ ዝግጁዎች እንሁን!!!

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ!!!

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የገጠመውን የገንዘብ እጥረት ለመወጣት ህዝቡን የመዝረፍ እንቅስቃሴውን ቀጥሏል

ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስፈልገውን እና በበርካታ ኢኮኖሚስቶች የውድቀት ትንቢት የተነገረለትን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተብዬ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ያለው የወያኔ አገዛዝ ከአሁኑ የገንዘብ እጥረት እንዳለበት ሲያመላክት እንደቆየ ዘገባዎች አመልክተዋል።

ከዚህ ቀደም የአገዛዙ ዋና አበዳሪ ከሆኑት ተቋማት ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀማጭ ገንዘብ ቀውስ ላይ እንደሚገኝ መዘገባችን ይታወሳል። በቅርቡም የአዲስ አበባ መስተዳደር የከተማይቱ ህዝብ ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር እንዲያዋጣለት በመጠየቅ የጠራራ ጸሃይ ዘረፋ እያሰናዳ መሆኑ በሰፊው ተዘግቧል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ተከታይ ዘገባ፥ የዘረኛው አገዛዝ ካድሬዎች ህዝቡ ገንዘብ የማጠራቀም ባህል እንዲያዳብር በመወትወት ላይ ናቸው። ዘጋቢያችን ያናገራቸው የመዲናይቱ ነዋሪዎች፥ "እኛ እንኳን የምናኖረው፤ የምንበላውም የለን" ሲሉ ስሞታቸውን አቅርበዋል።

አገዛዙ ህዝቡ ገንዘብ የማኖርን ባህል እንዲያዳብር በመምከር ሽፋን የንግድ ባንክን ካዝና ለመሙላት እና በተዘዋዋሪም ዝርፊያውን ለማጠናከር እቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ከዚህ ቀደም ባቀረብናቸው ዘገባዎች ጠቅሰናል። የቀድሞ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር ፕሬዚደንት እና የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከሁለት አመታት በፊት ባወጡት ጽሁፍ፣ በወያኔ ቁጥጥር ስር ያሉ ባንኮች አስቀማጮችን እያደኸዩ፣ ከአገዛዙ ጋር የተመሳጠሩ ነጋዴዎችን ሃብታም እያደረጉ መሆናቸውን ማስረዳታቸው ይታወሳል።

## የወያኔ አገዛዝ የአዲስ አበባን ህዝብ ለመበዝበዝ የሚያደርገው ስንድት ምሬት ቀሰቀሰ

የአዲስ አበባ መስተዳደር፥ የመጪው አምስት አመታት እቅዱን በገንዘብ በመደገፍ ስም ነዋሪው ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር እንዲያዋጣለት እቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የተለያዩ ዘገባዎች አመልክተዋል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ በላከው ተከታይ ዘገባ፥ አንዳንድ ነዋሪዎች፣ "ልጆቻችንን የምናበላው አጥተን ባለንበት ዘመን ከየት አምጥተን እንድንሰጣቸው ፈለጉ?" ሲሉ ተደምጠዋል። በከተማይቱ ውስጥ ሰባት መቶ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ማእከላት መመስረታቸውን የገለጸው ዘጋቢ፤ ነዋሪዎች ባለፈው እሁድ ስብሰባ ቢጠሩም ከካድሬዎች በስተቀር አብዛኛው ህዝብ እንዳልተገኘ አመልክቷል።

የአዲስ አበባ የገቢ ቢሮ፥ ህዝቡ ገንዘቡ ምን አይነት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን እንዲረዳ የከተማይቱን በጀት በዝርዝር ለህዝብ ማሳወቁን ተናግሯል። ይሁን እንጂ፥ ይህንን በሚመለከት ዘጋቢያችን ያናገራቸው ዜጎች፣ ይህ አገዛዙ ተጠያቂነት እንዳለ በማስመሰል ህዝቡን ለመዝረፍ ያዘጋጀው ማታለያ ነው ብለዋል።

የሚሰጡት ገንዘብ እንደሌላቸው የሚናገሩት ነዋሪዎች፤ ኖሯቸው ቢሰጡ እንኳ የት እንደሚሄድ እንደሚያውቁ እና ያም ወደካድሬዎቹ ኪስ ነው ሲሉ ገልጸዋል። ከዚህ የሚጠቀሙት የወያኔ ካድሬዎች ራሳቸው ስለሆኑና፣ የህዝብን ሃብት በመበዝበዝ የከበሩትም እነሱው በመሆናቸው፤ አስተዳደሩ እነሱኑ ቢጠይቅ ይሻለዋል ሲሉም አስተያየት ሰንዝረዋል።

## የኢትዮጵያ መሬት ለባዳ መቸርቸሩን ቀጥሏል፤ የህንዱ ካራቱሪ ከአንድ የአሜሪካ ግዛት የሚበልጥ መሬት ተሰጠው

የኢትዮጵያ ገበሬዎች በአማካይ ከአንድ ሄክታር ባነሰ መሬት ላይ እያረሱ በድህነት በሚማቅቁበት፤ ትላልቅ የእርሻ መሬቶች ለባዳ አገር ነጋዴዎች ነፃ ማለት በሚቻል ዋጋ መቸርቸራቸውን ቀጥለዋል።

በአለም አንደኛ የአበባ አምራች የሆነው የህንዱ ካራቱሪ ኩባንያ በጋምቤላ ክልል ከሶስት መቶ ሺህ ሄክታር በላይ፤ ወይም ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ጋሻ መሬት፤ ተሰጥቶት በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ቢዝነስ ዊክ የተባለው የዜና አውታር ዘግቧል። ይህ መሬት "ሮድ አይላንድ" ከተባለው የአሜሪካ ግዛት እንደሚበልጥም አመልክቷል።

ካራቱሪ ከዚህ ቀደም ሌላ መሬት ተሰጥቶት አበባ በማምረት ላይ እንዳለም ለማወቅ ተችሏል።

በርካታ የህንድ ኩባንያዎች በገዛ አገራቸው ያለውን የዜጎች መብት ጥበቃና የቢሮክራሲ ችግር፤ እንዲሁም ከሌሎች ኩባንያዎች የሚገጥማቸውን ውድድር ሸሽተ ወደ አፍሪካ እያመሩ እንዳለ ቢዝነስ ዊክ ገልጿል። አንዳንዶቹ ኩባንያዎች፥ የህንድ ዜጎች መሬታቸውን አልለቅ እያሉ ስላስቸገሯቸው፤ የዜጎች መብት ወደማይጠበቅባቸው የአፍሪካ አገራት እየጎረፉ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል።

ከዛ በተጨማሪም፥ ህንድ እና ቻይና ካላቸው ከፍተኛ የህዝብ ብዛት የተነሳ እንደ መሬት ያሉ የተፈጥሮ ሃብቶችን ፍለጋ ያሰፈሰፉ በመሆናቸው፤ ለገዛ ዜጎቻቸው ደህንነት እና እጣ ፈንታ ግድ ከሌላቸው የአፍሪካ ገዢዎች ዘንድ ዝምድናን አግኝተዋል። ከነዚህ የአፍሪካ አገራት ውስጥም በወያኔ ቁጥጥር ስር የምትገኘው ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ሆናለች።

ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ እስካሁን በርካሽ ዋጋ ወይም በነጻ ከቸረቸረው መሬት በተጨማሪ፣ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ሶስት ሚሊዮን ሄክታር፣ ማለትም ሰባ አምስት ሺህ ጋሻ መሬት ወይም ቤልጂየምን የሚያክል መሬት፣ ለባዳ አገር ነጋዴዎች ለማከፋፈል በዝግጅት ላይ እንዳለ መዘገቡ ይታወሳል።

ከነዚህ ውስጥ ለአበባ ነጋዴዎች የሚሰጡት መሬቶች ባብዛኛው በነጻ ሲሆን፤ የአበባ እርሻዎች ከሚጠቀሙት መርዛማ እና ከፍተኛ መጠን ያለው ማዳበሪያ የተነሳ መሬቶቹ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ዋጋ ቢስ እንደሚሆኑ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በተያያዘ ዜና ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች በጋምቤላ ከመሬታቸው እንዲፈናቀሉ እየተደረገ ነው

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ሆን ብሎ የባዳ አገር ነጋዴዎች የኢትዮጵያን መሬት እንዲቀራመቱ ማድረጉን ተከትሎ፤ ለመጤዎቹ መንገድ እንዲለቁ የጋምቤላ ገበሬዎችን እያፈናቀለ መሆኑን ዘገባዎች አመልክተዋል።

የጋራ ንቅናቄ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የተባለው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት የጋምቤላ ገበሬዎች ቤታቸውን እንዲለቁ እየተደረጉ ናቸው ሲል መግለጹን ብሉምበርግ የዜና አውታር ዘግቧል። የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከኢትዮጵያ ባስተላለፈው መረጃ እንዳስታወቀው፥ በአሁኑ ሰአት ገበሬዎቹን የማፈናቀሉን ስራ እንዲያስፈጽሙ የተመደቡት ካድሬዎች ነዋሪዎቹን እያስገደዱ ለእርሻ ወደሚያስቸግር አካባቢ እያሰፈሩ ነው።

የወያኔ አገዛዝ ጫካ በነበረበት ዘመን በወቅቱ አገዛዝ ሲፈጸም የነበረን ሰፈራ ክፉኛ ይቃወም እንደነበር ዘጋቢያችን አስታውሷል። በአካባቢው ከአንድ የአሜሪካ ግዛት የሚበልጥ መሬት የተሰጠው ካራቱሪ፣ ልክ እንደ ወያኔ፣ አንድም የተፈናቀለ ገበሬ የለም ሲል ሽምጥጦ መካዱን ብሉምበርግ በዘገባው አመልክቷል።

የህንድ ኩባንያዎች የገዛ አገራቸው ዜጎች መሬቶቻቸውን አልለቅ ብለው ለመብታቸው ስለቆሙ፤ የዜጎች መብት ወደማይጠበቅባቸው የአፍሪካ አገራት እየፈለሱ መሆኑን ቢዝነስ ዊክ ዘግቧል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በተለይ ባለፉት አምስት አመታት ገበሬዎችን እና የከተማ ነዋሪዎችን ያለ ተገቢ ካሳ በግፍ እያፈናቀለ መቆየቱ ይታወቃል። ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ለሸራተን ሆቴል መስፋፊያ እንዲሆን ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲፈናቀሉ የታዘዙ ነዋሪዎች ፍትህ ለመለመን ያዘጋጁት ሰላማዊ ሰልፍ መታፈኑን መዘገባችን ይታወሳል።

## አትሌት ሃይሌ ገብረስላሴ ከወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ሃይሌ ገብረስላሴ ባለፉት አምስት አመታት የወያኔን ጉዳይ የሚያስፈጽመው የሽማግሌዎች ቡድን አባል ሆኖ ከመቆየቱ በተጨማሪ፤ በመስከረም ወር በአዳማ በተካሄደው የገዢው ቡድን ጉባኤ ላይ ተገኝቶ የድጋፍ ንግግር ማድረጉና ለዘረኛው አምባገነን ስጦታ ማበርከቱ ይታወሳል። ሬከርድ ሲሰብር ለብሶት የነበረውን ከነቴራ ለመለስ ዜናዊ የሰጠበት ምክንያት ምን እንደሆነ በፍትህ ጋዜጣ የተጠየቀው ታዋቂ አትሌት፤ አምባገነኑ ስጦታው እንደሚገባው ገልጾ፣ መጽሃፍ ቅዱስም ቢሆን ንጉስህን አክብር ይላል ሲል ተናግሮ ነበር።

ወደፊት የፖለቲካ መሪ የመሆን ፍላጎት እንዳለው በግልጽ ተናግሮ የነበረው የእስፖርት ሰው፣ ከዘረኛው አገዛዝ ጋር የፈጠረው ቅርበት በህዝብ ዘንድ ባልጠበቀው መንገድ ከፍተኛ ቅሬታን እንዳስከተለበት ሲረዳ የስሜት መረበሽን ፈጥሮበት እንደነበር ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የአትሌቱን የቅርብ ምንጮች ጠቅሶ ባለፈው አርብ ዘግቦ ነበር። ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ኒው ዮርክ ታይምስ ለሃይሌ እና ለማናጀሩ ማስተባበያ መልስ አልሰጠም። ይሁን እንጂ በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች፥ ሃይሌ ጉዳዩን እንዲክድ በወያኔ ባለስልጣናት ጫና እንደሚደረግበት አስቀድመው ግምታቸውን ሲገልጹ ነበር።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org